# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## <u>ዜና ዘገባ</u>

**ግንቦት 12 ቀን 2005 ዓ.ም**

**የብአዴኑ ፍትሕ ሚኒስትር የነበረው የተባረረው በወያኔ ባለስልጣናት**

**ውሳኔ በመሆኑ ብአዴኖችን አስደንግጦዋል፤**

**የወያኔ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ድንገተኛ ስብሰባ ቢያደርግም የረባ ውጤት ሳመታ ተበትኗል፤**

**በባህር ዳር ተቀምጦ የነበረው የፌዴራል ፖሊስ ሰራዊት በሕዝቡ ቁጣ እንዲወጣ መደረጉ ተጠቆመ፤**

ለ21 ዓመታት ስልጣኑን ተቆጣጠሮ የነበረው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ከሞተ ወዲህ በወያኔና በተለጣፊ ድርጅቶቹ መከከል ተፈጠሮ የነበረው ሽኩቻ እና ንትርክ አድጎ ሰሞኑን አንዳንድ መልክ ማሳየቱ ታውቀዋል።

ወያኔ በባህርዳር ባደረገው 9ኛ ጉባዔም ላይ በወያኔ እና በብአዴን መሀከል የነበረው ከፍተኛ ፍጥጫ እና ንትርክ በወያኔ የበላይነት መመራት መጀመሩን የሚያሳዩ ምልክቶች እየታዩ መጥተዋል ተብሎዋል።

በባህር ዳር ከተማ ጉባኤ ከመከናወኑ አስቀድሞ አራቱም ድርጅቶች በተናጠል ባደረጉት ስብሰባ የየራሳቸውን እርምጃ የወሰዱ ሲሆን ወያኔ ነባርና ታዋቂ የነበሩ አመራር አባላቱን ከስራ አስፈጻሚነት እና ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት ሲያስወግድ ብአዴን የተባረረውንና የተሰናበተውን አዲሱ ለገሰን ወደ ስራ አስፈጻሚነት መልሶ በማስቀመጡ የተበሳጩ የወያኔ ባለስልጣናት ባነሱት አተካሮ የተነሳ በብአዴንና በህወሀት መሀከል ብጥብጥ ተከስቶ እንደነበር የሚታወስ ሲሆን ይሄንኑ ተከትሎ ወያኔ ውስጥ ውስጡን ተጠናክሮ በመቀጠል በቅርቡ አንዳንድ እርምጃዎች መውሰድ መጀመሩን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አስረድቶዋል።

በዚህም መሰረት በአሁኑ ሰዓት ከደኢህዴኑ ኃይለማርያም ደሳለኝ ጀርባ ሆነው ሀገሪቱን እና ፓርቲውን እያሽከረከሩ የሚገኙት የህወሀት ነባር እና ቱባ ባለስልጣናት በተለይ አባይ ጸሀዬ፤አባይ ወልዱ፤ጌታቸው አሰፋ፤ስብሀት ነጋ የሚገኙበት ቡድን ማክሰኞ ሚያዝያ 29 ቀን 2005 ዓ.ም በመቀሌ ከተማ ባደረገው ምስጢራዊ ስብሰባ የብአዴኑን የፍትህ ሚኒስትር ብርሀን ኃይሉን ከስልጣኑ እንዲባረር ያደረገ መሆኑ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች ከተገኘ ጥቆማ ለማወቅ ተችሏል::

መቀሌ ላይ በምስጢር ውሳኔው ከተሰጠ ከሁለት ቀናት በሁዋላ የብአዴኑ ብርሀን ኃይሉ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዘጠኝ ወር የስራ ሪፖርት ባቀረበ በ30 ደቂቃ ውስጥ ቢሮው የመሰናበቻ ደብዳቤ ቀድሞ እንደደረሰው እና ያለ አንዳች ጥያቄ ለቅቆ እንዲወጣ መደረጉንም ይሄው የደረሰን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አብራርቶዋል::

የፍትህ ሚኒስትሩ የብአዴኑ ሰው ብርሀን ኃይሉ በኃይለማርያም ፊርማ ከስልጣኑ ተባረረ ከመባል ባሻገር አንድም  ምክንያት ያልተሰጠው መሆኑን የታወቀ ሲሆን በምትኩ የህወሀቱ ልዑል ካህሳይ የተባለው ቦታውን እንዲቆጣጠረው መደረጉንም ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል::

መለስ ከሞተ በሁዋላ ወያኔ ተዳከመ ብአዴን ነገሰ ተብሎ በሰፊው ሲወራ የሰነበተ ቢሆንም ወያኔዎች መልሰን እናንሰራራለን እያሉ በመቀሌ ...በአዲግራት... በሽሬ.... በአክሱም..... በክልተ አውልአሎ..... በአድዋ..... እንዲሁም በሌሎች የትግራይ ክልል ከተሞች እና በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ የመንግስታዊ ተቋዋሞች ውስጥ ለአባሎቻቸው ቅስቀሳ ሲያደርጉ የቆዩ መሆናቸው ታውመቁ:: ባሉት መሰረት ውስጥ ውስጡን እየሰሩ አንገታቸውን ቀና ማድረግ ከመጀመራቸውም ባሻገር ብአዴንን ጨርሶ ለማዳከም እና አሁንም እኛው ነን ለማለት ግለሰቡን ከፍትህ ሚኒስትርነቱ ያለ አንዳች ምክንያት እንዲባረር አድርገው የራሳቸውን ሰው መሾማቸው የሚያመላክተው ከተሰጠው ግምት ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ነው የሚሉ ወገኖች ብዙዎች ናቸው::

በተለይ በእነ እስክንድር ነጋ ዙሪያ የብአዴኖቹ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች እና የወያኔዎቹ ዓቃቤ ሕጎች ውዝግብ እና ንትርክ ተከትሎ ግለሰቡ ጉዳዩን አስተባብሎና ሽብርተኛ መሆናቸውን አስረግጦ መግለጫ እንዲሰጥ ተነግሮት የነበረ ቢሆንም መግለጫ ሳይሰጥ በመቅረቱ አማራነቱ አይሉብታል የሚል ታፔላ ተለጥፎበት ከመቆየቱም በተጨማሪ ሌላ ምስጢራዊ ትዕዛዝ ብንሰጠውም ተግባራዊ ሊያደርግ አይችልም ከሚል ፍራቻ የተነሳ እንዲሁም ብአዴንን ማዳከም አንዱ መንገድ ሆኖ ስላገኙት እርምጃውን ሊወስዱ ችለዋል ሲሉም የውስጥ አዋቂ ምንጮች ይናገራሉ::

ተሰናባቹ የፍትህ ሚኒስትር ብርሀን ኃይሉ የአማራ ክልል የሰሜን ሸዋ ዞን የደብረ ብርሀን ከተማ ተወላጅ ሲሆን በመጀመሪያ የዞኑ አስተዳዳሪና የክልሉ የጤና ቢሮ ኃላፊ ከዚያም የማስታወቂያ ሚኒስትር ሆኖ ሲሰራ የቆየ ከመሆኑም በላይ ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ሲፈርስ ወደ ፍትህ ሚኒስትርነት እንደተዛወረም የስራ ግለ ታሪኩ ያስረዳል::

በበረከት ስምኦን አቅራቢነት በመለስ ዜናዊ ፊርማ የተሾሙ የከተማ ወጣት የብአዴን ካድሬዎች ከምንግዜውም በላይ በወያኔ ጫና እያረፈባቸው በመሆኑ አንዳንዶቹ ስራ እየለቀቁ ሲሆን

ሌሎቹ ደግሞ ለሊቀመንበሩ ተብየው ለደመቀ መኮንን ቅሬታቸውን በደብዳቤ አቤቱታ እያቀረቡ መሆኑ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚደርሱት ዜናዎች ይጠቁማሉ::

ይህ በእንዲህ እንዳለ የወያኔ ባለስልጣኖች የብአዴኑ ባለስልጣንና የአዲስ አበባ ምክር ቤት አባሉን መላኩ ፈንታን በሙስና ሰበብ ዘብጥያ ማውረዳቸው ታወቀ::

ሰሞኑን የብአዴኑ የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር መላኩ ፈንታን ጨምሮ 24 ባለሀብት እና ነጋዴዎች ከያሉበት ተለቅመው ለእስር የተዳረጉት በህወሀቶቹ አባይ ፀሀዬ ...አባይ ወልዱ...ጌታቸው አሰፋ.....እና በሌሎችም የህብረት ትዕዛዝ መሆኑንም ከተገኘው ዜና ማወቅ ተችሏል::

የብአዴኑ የገቢዎች እና የጉምሩክ ባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር መላኩ ፈንታን ጨምሮ 26ቱ እስረኞች ከዓርብ ግንቦት 2 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ከያሉበት እንዲለቀሙ የተደረገ ሲሆን ሌሎችም ሊያመልጡ ሲሉ ተያዙ ተብሎ ማዕከላዊ ምርመራ ጨለማ እስር ቤት ውስጥ ለአንድ ቀን ቆይተው ወደ ቃሊቲ እስር ቤት መወሰዳቸው ታውቆዋል::

በባህር ዳሩ 9ኛ ጉባኤ ላይ ስለ መልካም አስተዳደር መዳከም እና ስለ አማራው መፈናቀል አስተያየት ሲሰጥ የነበረው በተለይ በህወሀት የሚደገፉ ነጋዴዎች አላሰራ አሉኝ ብሎ በይፋ የተናገረው የብአዴኑ መላኩ ፈንታ በህወሀቶች ጥርስ ተነክሶበት ከቆየ በሁዋላ በብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቢሮ ልዩ ክትትል ሲደረግበት ቆይቶ ለእስር እንደተዳረገ ታውቋል::

ከዚሁ ከብአዴኑ ባለስልጣን ጋር የተያዘው የገቢዎች እና የጉምሩክ ባለስልጣን ምክትል ዳይሬክተር የሆነው ገብረዋህድ ወ/ጊዮርጊስ የተባለው የህወሀቱ ባለስልጣን በሚሊዮን የሚቆጠር ብር እና የቤት ካርታ በቤቱ ሸሽጎ ተገኘ ተብሎም ከቢሮው ተይዞ ለእስር መዳረጉ ታውቆዋል::

ከአዜብ መስፍን ጋር የቀረበ የንግድ ስራ ግንኙነት እንደነበረውና በሁዋላም ንብረቱ ተቀምቶ የተባረረው የኬኬ ንግድ ተቋዋም ባለቤት ከተማ ከበደም ከዚሁ ከመላኩ ፈንታ ጋር ግንኙነት አለው በሚል ጥርጣሬ በፖሊስ ተይዞ ዘብጠያ መውረዱ የታወቀ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት የፌዴራል ፖሊስ የአድማ ብተና ዋና መምሪያ አዛዥ የሆነችውና ብቸኛ የሴት ጄኔራል የአለምጸሀይ ካሣ የእህት ልጅ የሆነው የነጻ ትራንስፖርት ድርጅት ባለቤት ነጋ ገብረ እግዚአብሔርም በተመሳሳይ ከገብረዋህድ ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለው በሚል ለእስር መዳረጉን ከውስጥ ከተገኘ ዜና ለማወቅ ተችሏል::

በአስም ህመም ሲሰቃይ ነበር የተባለውና ለእስር ከመዳረጉ ጥቂት ቀደም ባሉት ቀናት በድሬዳዋ ቤት ገዝቶ የመኖሪያ አድራሻ ለውጥ ለማድረግ በዝግጅት ላይ ነበረ የተባለው የኬኬ ትሬዲንግ ባለቤት ከተማ ከበደ ዩዲ የተሰኙ ገልባጭ መኪኖችን ከአዜብ መስፍን ጋር በሽርክና እያስመጣ ሲሸጥ የነበረ መሆኑ የታወቀ ሲሆን የታሰረው በሙስና ነው ከተባለ አዜብም አብራ ዘብጥያ መውረድ ነበረባት የሚል አስተያየት በርካታ ወገኖች ይሰጣሉ::

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቢሮ ለዓመታት ሲከታተላቸው ነበር ተብሎ የተያዙት የወያኔ ባለስልጣናት ...ባለሀብቶች እና ነጋዴዎች በሶስት ምድብ እንደየቅርበታቸው ተከፍለው ድልድል የተሰጣቸው ሲሆን አንደኛው ምድብና እስከ አሁን ምንም ነገር ያልተኘበት መላኩ ፈንታ የሚመራው

ሲሆን ሁለተኛው ምድብ ደግሞ ምክትል ዳይሬክተሩና በሚሊዮን የሚቆጠር ብር በቤቱ ሸሽጎ ተገኘ የተባለው ገብረዋሀድ እንደሆነና ሶስተኛው ደግሞ በአፋሩ ተወላጅ መሀመድ ኢሳ የሚመራ መሆኑ ተገልጾዋል፡፡

በመላኩ ፈንታ ስር የተደለደሉት ባለስልጣንና ባለሀብቶች የባለስልጣኑ ዋና ዓቃቤ ህግ እሸቱ ወልደ ሰማያት ....የቃሊቲ ጉምሩክ ኃላፊ አስመላሽ ወ/ማርያም..... የኬኬ ባለቤት ከተማ ከበደ .....የኢንተር ኮንቲኔንታል ሆቴል ባለቤት ስማቸው ከበደ.....መርክነህ ዓለማየሁ እና ዶ/ር ፍቅሩ ማሩ የተሰኙት መሆናቸው ታውቆዋል፡፡

ሰራተኛውን እንደጥራጊ ሲያንቁዋሸሽ እና ሲያዋርድ የነበረው የገቢዎች እና የጉምሩክ ምክትል ዳይሬክተር በህወሀቱ ሹመኛ ገብረዋህድ ወ/ጊዮርጊስ ስር የተደለደሉት ባለስልጣናት..... ባለሀብቶች እና ተራንዚተሮች ደግሞ የተወረሱ ንብረቶች አስተዳደር ቡድን መሪ ጥሩነህ በርታ..... የናዝሬት ጉምሩክ ኃላፊ አሞኘ ታገለ.....በኦሮሚያ ልዩ ዞን መሐንዲስ ሙሉጌታ ጋሻው.....የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ምክትል ፕሬዝዳንት እንዲሁም የነጻ ትሬዲንግ ባለቤት ነጋ ገብረ እግዚአብሔር....የስዬ አብርሀ ወንድም ምሕረተዓብ አብርሀ.....የገብረዋህድ ወ/ጊዮርጊስ ባለቤት የመከላከያ ከፍተኛ መኮንን ኮ/ል ሀይማኖት ተስፋይ......በላቸው በየነ.....ተስፋዬ በየነ.....ሀብቶም ገ/መድህን እና የገብረዋህድ ባለቤት እህት የሆነችው ወ/ሮ ንግስቲ ተስፋይ እንደሚገኙበት ዝርዝሩ አጋልጦዋል፡፡

በናዝሬቱ የጉምሩክ ባለስልጣኑ መሀመድ ኢሳ ስር ደግሞ ትራንዚተር እና ኮሚሽን ሰራተኞቹ ዘሪሁን ዘውዴ እና ማርሸት ተስፋዬ......ሰመረ ንጉሴ...ሙሉቀን ተስፋዬ እና ዳኜ ስንሻው መሆናቸውም ታውቆዋል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ በጋምቤላ በኩል ወደ ሱዳን ሊኮበልል ነበር የተባለውና የናዝሬት ጉምሩክ የህግ ማስከበር ኃላፊ ተመስገን ጉልላት እና ተባባሪው የጋምቤላ ጉምሩክ ኃላፊው ጌታቸውም በቁጥጥር ስር ውለው ማዕከላዊ እስር ቤት መግባታቸውን የፌዴራል ፖሊስ ልዩ ጥበቃ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል፡፡

ከጥቂት የህወሀት ባለስልጣናት በስተቀር በብዛት የሚዘርፉት የወያኔ ባለስልጣናት አለመደይዛቸው ጥርስ የሌለው አንበሳ የተባለውና ባዶ ፕሮፓጋንዳ የሚነዛው የጸረ ሙስና ኮሚሽን በወያኔ ተፅእኖ ስር መውደቁን በግልፅ ያሳያል የሚሉ ብዙ ናቸው፡፡፡፡

ትዕዛዙ ወጪ ተደርጎ ባለስልጣናቱን በቁጥጥር ስር ለማዋል በተደረገው ስውር ዘመቻ የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ልዩ የፌዴራል ፖሊስ አባሎች እና ደህንነቶች ብቻ በመስሪያ ቤቱ በመገኘት ገሚሱ በአጥር ላይ ዘልለው ሌሎቹ ደግሞ በየመስኮቱ እየገቡ የአፈና ተግባር የፈጸሙባቸው ሲሆን በተለይ መላኩ ፈንታ በተያዘበት ወቅት ግራ እንደተጋባና የሆነውን ሁሉ ለማወቅ ተቸግሮ እንደነበረም ምንጮች አጋልጠዋል፡፡

በሚሊዮን የሚቆጠር የሀገር ውስጥ ብር እና በመቶ ሺህ ብር የሚቆጠር የተለያዩ ሀገራት ብሮች እንዲሁም ከ20 በላይ የቤት ካርታ ከቤቱ የተገኘበት የወያው አባል ገብረዋህድ በበኩሉ እንደ ፌንጣ እየዘለለ ለማምለጥ ቢሞክርም ፈርጣማ ጡንቻ ባላቸው ሲቪል የለበሱ የልዩ ኃይሉ ወታደሮች

ቁጥጥር ስር ሊገባ እንደቻለና  በትግሉ መሀከልም ሁለት ሶስቴ በቡጢ ሆዱ ላይ እንደተመታ ከመስሪያ ቤቱ የዓይን እማኞች ለመረዳት ተችሎዋል::

ሰራተኞቹን ሲያንቁዋሽሽ እና ሲያስፈራራ የሚታወቀው ምክትል ዳይሬክተሩ የህወሀቱ ሹመኛ ገብረዋህድ ወ/ጊዮርጊስ በትግል ተይዞ እጁን በካቲና ታስሮ ለ30 ደቂቃ ያህል በሰራተኞቹ መሀከል እንዲቆም የተደረገ ሲሆን ግለሰቡ ወያኔ ወደ አራት ኪሎ ቤተመንግስት በገባበት ወቅት የበረሀ ታጋይ የሆኑትን ለማስተማር በደሞዝ የተቀጠረና ተራ መምህር ሆኖ በጅጅጋ ሲሰራ የነበረ መሆኑን ቅርበት ያላቸው ወገኖች ጠቁመው የወያኔ ተራ አባል በመሆን ለጥቂት ዓመታት  ካገለገለ በሁዋላ የጅጅጋ ጉምሩክ ሰራተኛ በመሆን ተቀጥሮ በጥቂት ዓመት ውስጥ ወደ ዋናው ጉምሩክ ባለስልጣን ምክትል ኃላፊነት ሊመጣ እንደቻለ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ሲናገሩ ተደምጠዋል::

የገብረዋህድ ወ/ጊዮርጊስ ባለቤት የሆነችው የመከላከያ አባልዋ ኮ/ል ሀይማኖት ተስፋይ በበኩልዋ ከታናሽ እህቱዋ ጋር በመሆን  የባለቤቱዋን ስልጣን መከታ በማድረግ የሀገር እና የህዝብ ሀብት ስትቦጠቡጥ እንደነበረች የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች ተናግረዋል::

ተጠርጣሪ የተባሉት የወያኔ ፖለቲካ ጠልፎ የጣላቸው የብአዴኑ መላኩ ፈንታና ሌሎችም በቤታቸው ውስጥም ሆነ በቢሮዋቸው ውስጥ አንዳችም የሰነድ ማስረጃ ያልተያዘባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ መላኩ ፈንታ የክልል ምክር ቤት አባል መሆኑ እየታወቀ እራሳቸው ያወጡትን ህግ ጥሰው ለእስር መዳረጋቸው የሙስናው ምክንያት ተለጥፎበት ይሁን እንጂ በወያኔ ውስጥ የጎላ ሽኩቻ መኖሩን በግልጽ ያጋለጠ ነው ተብሎዋል::

የሀገሪቱን እና የህዝቡዋን ሀብት እየዛቁ ከዑራኤል ጀምሮ እስከ መገናኛ... ከፍላሚንጎ  እስከ ቦሌ መድኃኒዓለም ድረስ ዘመናዊ ህንፃዎችን ገንብተው እያከራዩ  በአሁኑ ሰዓት አሉ የተባሉ ቱጃሮች የሆኑትን የወያኔ ባለስልጣናት እና ጄኔራሎች ወደ ጎን ትተው በእነዚህ ላይ ብቻ መነጣጠሩ የራሳቸውን ጉድ ለመደበቅና ሌሎችን ለማጥቃት ነው የሚሉ ብዙ ናቸው::

ተጠርጣሪ የተባሉት እነዚሁ ተከሳሽ ባለስልጣናት ፍርድ ቤት ቀርበው የቃል ክርክር አደረጉ ተብሎ ለዓርብ ግንቦት 9 ቀን 2005 ዓ.ም ከጠበቆቻቸው ጋር ተነጋግረው እንዲቀርቡ  ቀጠሮ የተሰጣቸው ቢሆንም የህወሀቱ ገብረዋህድ ወ/ጊዮርጊስ ብቻ እድሉ ሲሰጠው መላኩ ፈንታን ጨምሮ ሌሎቹ ከጠበቆቻቸው ጋር እንዳይገናኙ የቃሊቲ እስር ቤት የበላይ ጠባቂ አብርሀም ወ/አረጋይ ማገዱን ጠበቆቹ ሲናገሩ ተደምጠዋል::

በሌላ ዜና  ባለስልጣናት በሙስና ለእስር በተዳረጉበትና የፍትህ ሚኒስትሩም ከስልጣን በተባረረበት ወቅት እሁድ ግንቦት 4 ቀን 2005 ዓ.ም የኢሕአዴግ ሰራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ድንገተኛ ስብሰባ ማድረጉ ታውቆዋል::

36 አባላት ብቻ የሚገኙበት የኢሕአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባሎች ድንገተኛ ስብሰባ ያደረጉት በታሰሩት እና በተባረረው የብአዴን ባለስልጣናት ዙሪያ ለመነጋገር እና አቁዋማቸውን ለመግለጽ የነበረ ቢሆንም ባለመግባባት ስብሰባው መጠናቀቁን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አጋልጠዋል::

ስብሰባው አርሶ አደሩን ትርፍ አምራች ማድረግ በሚል የተጀመረ ቢሆንም በታሰሩት የብአዴን ሰዎች እና በፍትህ ሚኒስትሩ ዙሪያ በተነሳ እሰጥ አገባ በሁለቱም ወገን መደማመጥ እና መግባባት በመጥፋቱ ለሌላ ግዜ እንዲተላለፍ ተደርጎ መቁዋጨቱን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አብራርቶዋል::

በተደረገው እሰጥ አገባ ውስጥ ኦህዴዶች እና ደኢህዴኖች አንዳችም አስተያየት ሳይሰጡ የዳር ተመልካች ሆነው የዋሉ ሲሆን የህወሀቶቹ እና የብአዴኖቹ ግን መግባባት ላይ ሳይደርሱ መቅረታቸው ይወራል::

በመጨረሻም የወያኔ ቡድን በውስጡ በተፈጠረ ትርምስ እርስ በርስ እየተናከሰ ባለበት በዚህ ወቅት አንድ የስርዓቱ እድሜ አራዛሚ አንጋች የፌዴራል ፖሊስ ዘግናኝ በሆነ መልኩ በዜጎች ላይ የጅምላ ግድያ መፈጸሙ ታወቀ::

በቀድሞዋ የወያኔ ነባር ታጋይ በአሁንዋ ብቸኛ የሴት ጄኔራል አለምጸሀይ ካሣ የሚመራው የፌዴራል ፖሊስ የአደጋ መከላከል ስር የነበረው ይሄው ታጣቂ በባህር ዳር ከተማ እሁድ ግንቦት 4 ቀን 2005 ዓ.ም ለጥበቃ በተሰጠው ራሽያ ሰራሽ በሆነው ክላሽንኮቭ መሳሪያ ዜጎችን በጅምላ መግደሉ ታውቆዋል::

እሁድ ግንቦት 4 ቀን 2005 ዓ.ም ከምሽቱ 2 ሰዓት ተኩል ላይ የፌዴራል ፖሊስ አባል የሆነ አንድ ወታደር አባይ ማዶ ቀበሌ 11 ተብሎ በሚጠራው ሰፈር 14 ሰዎችን በእሩምታ ተኩስ ከፍቶ የገደላቸው ሲሆን ሌሎች 2 ሰዎች ደግሞ በጽኑ ማቁሰሉን ከባህርዳር የደረሰን ጥቆማ ገልፆዋል::

የወያኔ ስርዓት እየተዳከመና እየዳኸ ባለበት በዚህ ወቅት መልሶም ባለስልጣናቱ እርስ በርስ እየተሸኮቱ ባለበት በዚህ ግዜ በህዝብ ላይ አፈሙዝ እንዲደግን ባስተማሩት ወታደር ዜጎችን ያለ አንዳች ርህራሄ በጅምላ መግደሉ እጅግ አሳዛኝ እና ነውረኛ ተግባር ነው ሲሉ የባህርዳር ከተማ ነዋሪዎች በቁጭት ሲናገሩ ተደምጠዋል::

ሕዝቡ የወያኔን የአምባገነን ስርዓት በመቃወም በሰላማዊ መንገድ ተቃውሞ እንዳያሰማ ጭምር ከመቶ ሺህ በላይ የሆኑ የፌዴራል ፖሊሶችን በየከተማው በትኖ የህዝቡን ነጻነት አፍኖ መያዙ ሳያንሰው ግብረ ገብ ያልተማሩት እነዚሁ ታጣቂዎች በጅምላ ዜጎችን መረሸናቸው አሳፋሪና አሳዛኝ ነው ሲሉም የባህር ዳር ከተማ ነዋሪዎች እልህ እየተናነቃቸው ይናገራሉ::

የፌዴራል ፖሊሱ 30 ጥይቶችን በጎረሰው መሳሪያ ግድያውን የጀመረ ሲሆን ጥይቱ ሲያልቅበት እንደገና ሌላ ካርታ ቀይሮ እያፈራረቀ 14 ሰዎችን ሲገድል አብረው በጥበቃ ላይ የተሰማሩ አምሳያዎቹ ሳይከላከሉት ይልቁንም የዳር ተመልካች ሆነው እንደነበር የባህር ዳር ሕዝብ በመስማቱ ከፌዴራል ፖሊስ ጋር ግጭት መፍጠሩ ታውቆዋል::

የህዝቡ ቁጣ እያየለ መምጣቱን ያዩት የአማራ ክልል ባለስልጣናት በባህር ዳር ተቀምጦ የነበረው የፌዴራል ፖሊስ ሙሉ ለሙሉ ጉዋዙን ሸክፎ ከተማዋን በምሽት እንዲለቅ መደረጉንም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል::

ግድያውን የፈጸመው ይሄው የፌዴራል ፖሊስ አባሉ ግድያውን በፈጸመበት አቅራቢያ አባይ ወንዝ ውስጥ ዘሎ ገብቶዋል ተብሎ በሰፈሩ ዋናተኞች ሲፈለግ ቆይቶ በማግስቱ አስከሬኑ የተገኘ ሲሆን ቤተሰቦቹና የቅርብ ሰዎቹ ባልተገኙበት ቀብሩ የተከናወነ መሆኑንና በግፍ የተጨፈጨፉ ዜጎች ስርዓተ ቀብርም በከተማዋ በሚገኙ በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የተፈጸመ መሆኑ ታውቆዋል፡፡